
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መ/ቤት አጠቃላይ መግለጫ




አድራሻ


ወረዳ 2 ቀበሌ 15
አዲስ አበባ
ፖ.ሳ.ቁ 1143
ስልክ ቁጥር 55-30-11
ፋክስ 55-03-34
ኢሜል csadp@telecom.net.et



በማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት የተዘጋጀ

መስከረም 1994

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መ/ቤት አጠቃላይ መግለጫ




አድራሻ

*ወረዳ 2 ቀበሌ 15*
*አዲስ አበባ*
*ፖ.ሳ.ቁ 1143*
*ስልክ ቁጥር 55-30-11*
*ፋክስ 55-03-34*
*ኢሜል csadp@telecom.net.et*



በማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት የተዘጋጀ

*መስከረም 1994*

# ማውጫ


ገጽ

1. መግቢያ .......................................................................... 1
2. የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን አመሠራረት .......................... 2
3. የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት ......................3
4. የመ/ቤቱ ድርጅታዊ አወቃቀር ..................................................4
5. የስታቲስቲክስ መረጃዎች ጥቅምና አስፈላጊነት ...............................6
6. የስታቲስቲክስ መረጃዎች ለልማት ሥራዎች ያላቸው ሚና ..................7
7. የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች .......................................9
8. የስታቲስቲክስ ጥናቶች (ሥራዎች) አፈፃፀም ቅደም ተከተል ........... 10
    8.1 የቅድመ ዝግጅት ተግባራትን ማከናወን ................................ »
    8.2 መረጃ ከመስክ መሰብሰብ ................................................ 11
    8.3 መረጃ ቅንብር ............................................................ 12
    8.4 ሪፖርት ዝግጅት፣ ህትመትና ስርጭት .................................. »
9. ከመረጃ ሰጭዎች የሚጠበቅ ትብብር ..........................................13
10. የስታቲስቲክስ መረጃዎችን ማሠራጫ ዘዴዎች ................................14
11. መ/ቤቱ ካከናወናቸው አበይት ተግባራት .......................................15
12 በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ከ1987 ዓ.ም. ጀምሮ የተካሄዱ አጠቃላይ ቆጠራዎችና ናሙና ጥናቶች ዝርዝር ...............16
    12.1 ከ1987-1993 የተካሄዱ ከአጠቃላይ ቆጠራዎች፣ ከናሙና ጥናቶች የተሰበሰቡ መረጃዎች ................................ »
    12.2 በ1994 በመካሄድ ላይ ያሉ አጠቃላይ ቆጠራዎች፣ የማኀበራዊና የዲሞግራፊያዊ ናሙና ጥናቶችና ከአስተዳደር መዛግብት የተሰበሰቡ ወይም የሚሰበሰቡ መረጃዎች .........18
13 የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች .............. 22
14 አዲስ የተከፈቱ የማብርና ቆጠራ ጽ/ቤቶች ....................................24

# 1. መግቢያ

የአንድን ሀገር የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠንና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ የልማት ዕቅዶችንና ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች አስፈላጊ ናቸው።

የተዘጋጁት ዕቅዶችና ፖሊሲዎች በተግባር ላይ ሲውሉ የሚያስገኙትን ውጤት ለመከታተልና ለመገምገም እንዲቻልም በስርዓትና በግይንግዊ መንገድ የተሰበሰቡና የተቀነባበሩ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችና የጥናት ውጤቶች ተፈላጊነት ዕሙን ነው።

ይህንን እጅግ አስፈላጊ የሆነ ተግባር ከመፈፀም አኳያ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ዓለም አቀፍ የስታቲስቲክስ አሠራር መርሆዎችን መሠረት በማድረግና የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ በርካታ ጥናቶችን ከዳር በማድረስ ረገድ ውጤታማነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል። በኢኮኖሚያዊ፣ በማኅበራዊና በሥነ-ህዝብ መስኮች አጠቃላይ ቆጠራዎችንና የናሙና ጥናቶችን አካሂዶ ለተጠቃሚዎች በማቅረቡም በአገሪቱ ውስጥ የነበረውን የመረጃ ክፍተት ደረጃ በደረጃ በመቅረፍ ላይ ይገኛል።

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መ/ቤትን አመሠራረት፣ ዓላማ፣ ያሉበትን ኃላፊነቶች፣ ያከናወናቸውንና የሚያከናውናቸውን ተግባራት በተመለከተ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ይህ አጠቃላይ መግለጫ ተዘጋጅቷል ።

## 2. የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን አመሠራረት

በ1952 ዓመተ ምህረት መባቻ ላይ የመጀመሪያው የአፍሪካ ስታቲስቲሽያኖች ጉባኤ አዲስ አበባ ላይ ተካሂዶ ነበር፡፡ በዚህ ጉባኤ ማጠቃለያ ላይም እያንዳንዱ አባል አገር የአምስት ዓመት የስታቲስቲክስ ፕሮግራም በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲያደርግ ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ በመሆኑም በወቅቱ የንግድ፣ የኢንዱስትሪና ፕላን ሚኒስቴር ይባል በነበረው የሚኒስቴር መ/ቤት ውስጥ የአገሪቱን የስታቲስቲክስ ሥራ የሚያካሂድ ክፍል ተመስርቶ በዚሁ ዓመት ተግባሩን ጀመረ፡፡

- በ1964 ዓ.ም. በትዕዛዝ ቁጥር 79/1964 ራሱን የቻለ ድርጅታዊ አቋም ኖሮት የስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት በሚል ስያሜ ተቋቋመ፡፡

- ከ1971-1979 ለብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ተጠሪ በመሆንና በየክፍለ ሀገሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመክፈት ተጠናክሮ ሥራውን እንዲያስፋፋ ተደረገ፡፡

- በ1980 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 8/1980 መሠረትም ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ጽ/ቤት ሆኖ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የሚል ስያሜ ተሰጠው፡፡

- በ1987 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሲመሰረት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ተጠሪነቱ ለኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር (በአሁኑ ወቅትም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር) ሆኖ ተግባሩን በማከናወን ላይ ይገኛል።

## 3. የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት

የመሥሪያ ቤቱ አበይት ተግባራትና ኃላፊነቶች የሚከተሉት ናቸው።

3.1 የስታቲስቲክስ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተንና ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣

3.2 ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የሥነ-ሕዝብ መረጃዎች ማዕከል ሆኖ ማገልገል፣

3.3 ለመንግሥትና ለሌሎችም መረጃ ተጠቃሚዎች ስታቲስቲክስ አገልግሎት የሚውሉ የረዥም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የስታቲስቲክስ ዕቅዶች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እያዘጋጀ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ማዋል፣

3.4 ስታቲስቲክስን በሚመለከት መመሪያዎችና ደንቦች በሥራ ላይ መዋላቸውን፣ እንዲሁም የስታቲስቲክስ ተግባራት በሚከናወኑበት ጊዜ የወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች የሚከተሉ መሆናቸውን በተመለከተ ምክር መስጠት፣

3.5 የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የስታቲስቲክስ ሥራዎች ማስተባበርና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤

3.6 ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የአስተዳደር መዛግብት የሚገኙትን መረጃዎች በማጠናቀር ስታቲስቲካዊ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ማቅረብ፤

3.7 ከመንግሥትና ከሌሎችም መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ጠቅላላ ቆጠራዎችን ማካሄድ፤ እንደዚሁም የስታቲስቲክስ ጥናቶች እና ምርምሮችን ማዘጋጀትና መምራት፤

3.8 በጠቅላላ ቆጠራዎች ሥራ ወቅት የኮሚሽን ጽ/ቤት ሆኖ ማገልገልና ተግባሩን ማከናወን፤

3.9 ለስታቲስቲክስ አገልግሎት የሚውሉ የስታቲስቲክስ ትርጉምና አመዳደብ ማውጣትና አፈጻጸማቸውን መከታተል፤

3.10 የሚሠራባቸውን የስታቲስቲክስ አሠራር ዘዴዎች በየጊዜው በመገምገም ዘመናዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወኑ ማድረግ፤

3.11 በስታቲስቲክስ መረጃዎች ተጠቃሚ የሆኑ መሥሪያ ቤቶችንና ሌሎች ክፍሎችን ፍላጎት ለማርካት እንዲቻል በባለሥልጣኑ እና በተጠቃሚዎች መካከል የቅርብ ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር ሴሚናሮችና ስብሰባዎች በማካሄድ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ፤

3.12 ከሌሎች አገሮች ስታቲስቲክስ መሥሪያ ቤቶችና ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት መፍጠርና በዓለም አቀፍ ስታቲስቲክስ ፕሮግራሞች ተካፋይ ለመሆን አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ፣

3.13 ከመንግሥትና ከሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ጋር በመስማማትና በመተባበር እንዲሁም ውክልና በመቀበል የስታቲስቲክስ ሥራዎችና ፕሮግራሞችን ማከናወን፣

3.14 በስታቲስቲክስ ጉዳይ ሁሉ በጠቅላላው ለመንግሥት ምክር መስጠት፣

3.15 ከመንግሥት የሚተላለፉ ሌሎች ሥራዎችን ማከናወን ናቸው።

## 4. የመ/ቤቱ ድርጅታዊ አወቃቀር

የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በአሁኑ ወቅት:-

- አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ
- አንድ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ
- አንድ የሕዝብ ጉዳይ ጥናት ማዕከል ኃላፊ
- ስምንት ዓላማ አስፈጻሚ መምሪያዎችና
- አሥር አገልግሎቶች ያሉት ሲሆን 22 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችንና በአሁኑ ጊዜ በመካሄድ ላይ ያለውን የግብርና ናሙና ቆጠራ ለማስፈፀም 25 ተጨማሪ ጽ/ቤቶችን በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች አደራጅቷል።

## 5. የስታቲስቲክስ መረጃዎች ጥቅምና አስፈላጊነት

ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የሕብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ዲሞግራፊያዊ ሁኔታዎችን ሊያመለክቱ የሚችሉ አሀዛዊ መግለጫዎች ሲሆኑ ጥቅሞቹም የሚከተሉት ናቸው፡

5.1 የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል/ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን ለመንደፍ ያገለግላሉ፡፡

5.2 በነባራዊ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ የሕብረተሰቡን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችሉ የልማት ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት፣ ዕቅዶቹ ሲተገበሩም አፈጻጸማቸውን ለመከታተልና ለመገምገም ያገለግላሉ፡፡

5.3 በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በዲሞግራፊያዊ መስኮች አዲስ ወይም ቀጣይ ጥናቶችን/ምርምሮችን ለማካሄድ መነሻ/መሠረት ይሆናሉ፡፡

5.4 በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች የነበሩትን ወይም ያሉትን ክስተቶች ለማወዳደርና ለማነጻጸር ብሎም የወደፊቱን ለመተንበይ ይጠቅማሉ፡፡

5.5 በክልሎች መሀል የተቀራረበ ዕድገት ለማስፈን አሃዛዊ መረጃዎች ይጠቅማሉ፡፡

5.6 የግል ባለሀብቶች መዋዕለ-ንዋያቸውን በየትኛው የሥራ ዘርፍ፣ ምን ያህል፣ የት ቦታ ኢንቨስት ቢያደርጉ ይበልጥ

ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ በአመልካችነትና በመነሻነት ግልጋሎት ይሰጣል፡፡

5.7 ለጥናትና ለምርምር፣ ለአስተዳደር ጉዳዮች እና የምርጫ ሂደትን ለማስፈፀም ያገለግላሉ፡፡

## 6. የስታቲስቲክስ መረጃዎች ለልማት ሥራዎች ያላቸው ሚና

ስታቲስቲካዊ መረጃዎች በጥራት በጥልቀትና በስፋት ተሰብስበው፣ ተቀነባብረውና በሥርዓት ተከማችተው ሲገኙ የአንድን አገር ዕድገት ለማፋጠን ለሚቀየሱ የልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ዝግጅት ያላቸው ገላጭነት ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር፡-

6.1 በመንግሥትም ሆነ በግል ኢንቨስተሮች አማካይነት የሚዘረጉ የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታና የሚቀርቡ አገልግሎቶች የሕዝቡን አሠፋፈር፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ በሚያሳዩ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች፣ የጥናትና የምርምር ውጤቶች ላይ መመሥረት ስለአለባቸው፡፡

6.2 በግብርናው መስክ በምግብ ምርት አቅርቦት እራስን ለመቻልና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች ለመንደፍና የአፈጻጸሙን ሂደት ለመቆጣጠር የግብርና ስታቲስቲክስ መረጃዎች፣ የጥናትና የምርምር ውጤቶች ወሳኝ ሚና ስለአላቸው፡፡

6.3 የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ የማዕድንና ቁፋሮ ክፍለ ኢኮኖሚዎች እንቅስቃሴን የሚያሳዩ መረጃዎች፣ የጥናትና የምርምር ውጤቶች መኖር የዘርፉን ዕድገት ለማፋጠንና የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል ስትራቴጂ ለመቀየስ አስፈላጊ በመሆናቸው፣

6.4 የኮንስትራክሽን፣ የንግድ፣ የትራንስፖርትና መገናኛ ዘርፍ ለሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች እንቅስቃሴ በማገዝ በኩል እየተጫወቱ ያለውን ድርሻ ይበልጥ የተሟላ የሚያደርጉ መረጃዎችን ስለሚያቀርቡ፣

6.5 የሕዝቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ለመከታተል የሚያስችሉ ዝርዝር የምርቶች፣ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋ ኢንዴክሶችን ለማቅረብ ስለሚያስችሉ፣

6.6 የሕዝቡን ብዛት የየዓመት የወደፊት የዕድገት መጠን በማስላትና በመተንበይ ከአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት መጠን ጋር በተመጣጠነ መልኩ የሥነ-ህዝብና መስል ፖሊሲዎች ለመቅረጽና ለመተግበር አስፈላጊ የሆኑ ሕዝብ ነክ መረጃዎች የሚያስገኙ በመሆናቸው፣

6.7 የሕዝቡን ንፁህ የመጠጥ ውሃና የኃይል ምንጭ አቅርቦትን ለማሻሻል የሚረዱ መሠረታዊ መረጃዎች በመሰብሰብ በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ ለሚቀየሱት ፕሮጀክቶችና ስትራቴጂዎች ለመቅረጽ በመነሻነት ለመጠቀም ወሣኝ ሚና ስላላቸው፣

6.8 ለኢኮኖሚ ግንባታ ወሣኝ ሚና የሚጫወቱትን የትምህርትና የጤና አገልግሎት ሽፋን ለመገምገም ብሎም ሽፋኑን ለማሳደግ የሚያስችሉ መረጃዎች ስለሚያቀርቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ለልማት ሥራዎች ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው።

## 7. የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

የስታቲስቲክስ መረጃዎችን አጠናቅሮ፣ ተንትኖና በተለያየ መልክ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ለማሠራጨት በቅድሚያ መረጃዎችን የመሰብሰብ ተግባር መከናወን ይኖርበታል። ይህን ተግባር ማከናወን ከሚያስችሉ ዘዴዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

7.1 አጠቃላይ ቆጠራዎች (CENSUSES)

- አጠቃላይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ (Population and Housing Census)
- አጠቃላይ የግብርና ቆጠራ (Agricultural Census)
- አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ቆጠራ (Industrial Census) ወዘተ

7.2 ናሙና ጥናት (Sample Survey)

7.3 የአስተዳደር መዛግብት (Administrative Records) እና

7.4 የማያቋርጥ የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ (Continous Vital Statistical Registration) ናቸው።

## 8. የስታቲስቲክስ ጥናቶች (ሥራዎች) አፈጻጸም ቅደም ተከተል

የስታቲስቲክስን ጥናቶች ከላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች አካሂዶ ዳር ለማድረስ አራት የተያያዙ የአሰራር ሂደቶች ተግባራዊ ይሆናሉ። እነዚህም:-

### 8.1 የቅድመ ዝግጅት ተግባራትን ማከናወን

ሀ. የጥናቱን ዓላማ፣ ጥቅምና አስፈላጊነት፣ እንደዚሁም የሰው ኃይልና የበጀት ፍላጎትን የሚያመለክት የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ማዘጋጀት፣

ለ. የጥናቶቹን ዓላማዎች ለማሟላት መሰብሰብ የሚኖርባቸውን የመረጃ ዓይነቶች መወሰን፣

ሐ. የተፈለጉ መረጃዎች ከምን/ከየት (ከቤተሰብ፣ ከግለሰብ፣ ከድርጅት፣ ከመሥሪያ ቤት፣... ወዘተ)፣ ሊገኙ እንደሚችሉ ማወቅ፣

መ. መረጃዎቹ የሚሰበሰቡበትን ዘዴ መቀየስ፣

ሠ. ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ዶክመንቶች ማለትም መጠይቆች፣ መመሪያዎች፣ ልዩ ልዩ ቅጾች እና ካርታዎች ማዘጋጀት፣

ረ. በጥናቱ መረጃ እንዲሰበስብባቸው በተዘጋጁ ቅጾችና መመሪያዎች ይዘት ላይ በዋና ዋና መረጃ ተጠቃሚዎች

አስተያየት እንዲዳብር የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በሴሚናር መልክ ማወያየት፤

ሰ. ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን በቅድሚያ አውቆ ተገቢ ስልት መቀየስ እንዲቻል የሙከራ ጥናት ማካሄድ፤

ሸ. ለጥናቱ የሚያስፈልጉ የሎጂስቲክስና የሌሎች ማቴሪያሎች ፍላጎትን ማሟላት፤

ቀ. ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ሠራተኞችን የመመልመል፣ የማሰልጠንና የማሰማራት ተግባራትን ማከናወን::

8.2 መረጃ ከመስክ መሰብሰብ

ሀ. ተፈላጊ መረጃዎችን በጥናቱ ከሚሸፈኑ የቆጠራ ቦታዎች ወይም ከአስተዳደር መዋቅቦት በተቀየሱ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ከግለሰብ፣ ከቤተሰብ ወይም ከድርጅቶች መሰብሰብ፤

ለ. ከመስክ በገጠር ወይም በከተማ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት የመረጃውን ጥራት ለመጠበቅ አስፈላጊውን የመስክ ቁጥጥር ማድረግ፤

ሐ. በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካይነት የተሞሉና መረጃ የተሰበሰበባቸው መጠይቆችና ቅጾች ብዛትና ይዘት የተሟሉ መሆናቸው ተረጋግጦ ወደ ዋናው መ/ቤት እንዲተላለፍ ማድረግ::

## 8.3 መረጃ ቅንብር

ሀ. ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ኮምፒውተር ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ለቅንብር በሚያመች ሁኔታ የኤዲቲንግና የኮዲንግ ሥራ ማከናወን፣

ለ. አሀዛዊ መረጃዎችን ኮምፒውተር ውስጥ ማስገባት፣

ሐ. በኮምፒውተር አማካኝነት አሃዛዊ መረጃዎችን ከስሁተት የማጽዳትና የማገናዘብ ሥራ ማከናወን፣

መ. ለሪፖርት ዝግጅትና ትንተና የሚያስፈልጉ ሠንጠረዦች ማዘጋጀት፣

ሠ. በተዘጋጀው የሠንጠረዥ ፕላን (Tabulation plan) መሠረት የኮምፒውተር ፕሮግራም በመጻፍ የሠንጠረዥ ቅንብሮችን መሥራት።

## 8.4 ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ስርጭት

ሀ. በሠንጠረዥ የተዘጋጁትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ የጥናቱን ግኝት (Findings) በመገምገምና በመተንተን ዝርዝር ሪፖርት ማዘጋጀት፣

ለ. የጥናቱን ውጤት ለተጠቃሚዎች ለማስተዋወቅና ለማብራራት እንደ አስፈላጊነቱ ሴሚናሮችንና አውደ ጥናቶችን ማካሄድ፣

ሐ. የተዘጋጁትን ፎርሞች በበቂ ቅጅዎች በማተም ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት ፡፡

## 9. ከመረጃ ሰጭዎች የሚጠበቅ ትብብር

የስታቲስቲክስ መረጃ ምንጮች/ሰጭዎች በአጠቃላይ ሕብረተሰቡ፤ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶችና ድርጅቶች ናቸው፡፡ የሚሰበሰቡት መረጃዎች የኢኮኖሚያዊና የማኅበራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ ለሚቀየሱ ፖሊሲዎችና የልማት ዕቅዶች መሠረት ከመሆናቸውም ባሻገር ፖሊሲዎቹና የልማት ዕቅዶቹ በተግባር ላይ ሲውሉ አፈጻጸማቸውን ለመከታተልና ለመገምገም መነሻ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ስለሆነም መረጃዎች ለጋራ ጥቅም የሚውሉ መሆናቸው ግንዛቤ አግኝቶ፡-

9.1 ከግለሰብም ሆነ ከድርጅት የሚሰበሰቡ ማናቸውም ዓይነት መረጃዎች ሚስጥራዊነታቸው ፍፁም ስለሚጠበቅ፤

9.2 የሚዘጋጁት ስታቲስቲካዊ ፎርሞች በግለሰብ ወይም በድርጅት ደረጃ ሳይሆን በጥቅል የሚቀነባበሩና የሚወጡ ስለሆነ፤

9.3 ከላይ በተ.ቁ. 9.1 እና 9.2 በተገለፀው መሠረት፡-

- የሚሰበሰቡት መረጃዎች በሚስጥር የሚጠበቁ መሆናቸው ታውቆ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ስታቲስቲካዊ መረጃ እንዲሰጥ ሲጠየቅ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት በመረዳትና በሕግ ጭምር ስለተደነገገ፤

- መረጃ ሰብሳቢዎች ከግለሰቦችና ከድርጅቶች መረጃ እንዲሰጣቸው በሚጠይቁበት ጊዜ ትክክለኛ መረጃ በመስጠት በኩል ከሁሉም ዜጋ ከፍተኛ ትብብር ይጠበቃል::

## 10. የስታቲስቲክስ መረጃዎችን ማሠራጫ ዘዴዎች

በባለሥልጣን መ/ቤቱ የመረጃ አሰራጫጨት ልምድ መሠረት መረጃዎች ለአጠቃቀም በሚያመች ሁኔታና አቅም በፈቀደ መጠን በተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች ከተዘጋጁ በኋላ፦

10.1 የመረጃዎቹ ከፍተኛ ተጠቃሚ ለሆኑ መ/ቤቶችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በነፃ ይታደላሉ፤

10.2 በመ/ቤቱ ቅጽር ግቢ በተከፈተው ሽያጭ ክፍል መረጃ ፈላጊዎች በግዥ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

10.3 በመ/ቤቱ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ በቂ ቅጅዎችን በማስቀመጥና መረጃ ፈላጊዎችን ተቀብሎ በማስተናገድ ግልጋሎት ይሰጣል፤

10.4 እንደ አስፈላጊነቱም በኮምፒውተር ዲስኬቶች የጥናት ውጤቶችንም ሆነ የስታቲስቲክስ ሠንጠረዦችን መረጃ ተጠቃሚዎች ያገኛሉ፤

10.5 በውጭ ሀገር ለሚኖሩ መረጃ ጠያቂዎችም የፖስታ ወጪና የሪፖርቶችን ዋጋ እንዲሸፍኑ /እንዲከፍሉ በማድረግ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች እንዲደርሷቸው ይደረጋል::

## 11. መ/ቤቱ ከከናወናቸው አበይት ተግባራት

የስታቲስቲክስ ሥራ በአገራችን እንደ አንድ ሙያ ተቋቁሞ መሠራት ከጀመረበት ከ1952 ዓ.ም. አንስቶ ከአጠቃላይ ቆጠራዎች፣ ከናሙና ጥናቶችና ከአስተዳደር መዝገቦች የተገኙ በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ሕዝባዊ መረጃዎች በጥቅም ላይ ውለዋል ። እየዋሉም ናቸው። በዚህም መሠረት፦

11.1 ከ1973 ዓ.ም ወዲህ በሀገሪቱ የገጠር አካባቢዎች የተቀናጀ ብሔራዊ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም በማቋቋም የግብርና፣ የሰው ኃይል፣ [illegible]፣ የሥነ ሕዝብ፣ የኢንዱስትሪ፣ የዋጋ፣ የጤናና አመጋገብ ወዘተ. የናሙና ጥናቶችን እየሰራ ውጤቱን ለተጠቃሚዎች አሰራጭቷል።

11.2 በግንቦት 1976 የመጀመሪያውን በጥቅምት 1987 ደግሞ ሁለተኛውን ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራዎችን አካሂዷል።

11.3 [illegible] የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የግል ድርጅቶች ልዩ ልዩ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማጠናቀር እያለ ወቅታዊና ተከታታይነት ያላቸው መረጃዎችን በማውጣት የስታቲስቲክስ መጽሔቶች እያዘጋጀ ለተጠቃሚዎች አቅርቧል።

11.4 ስለ አገራችን በአስተዳደር ክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በገበሬ ማኅበርና በቀበሌ ቦታዎች ደረጃ፣ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ

ምልከቶችን የሚያሳዩ፣ መረጃዎችን የሚሠጡና ለሌሎች ጥናቶች እንደፍሬም የሚያገለግሉ ካርታዎችን በማዘጋጀት በነጻና በመጠነኛ ክፍያ ለተጠቃሚዎች አቅርቧል። ያቀርባልም።

## 12. በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ከ1987 ዓ.ም. ጀምሮ የተካሄዱ አጠቃላይ ቆጠራዎችና ናሙና ጥናቶች ዝርዝር

12.1 ከ1987-1993 የተካሄዱ ከአጠቃላይ ቆጠራዎች፣ ከናሙና ጥናቶች እና ከአስተዳደር መዛግብት የተሰበሰቡ መረጃዎች

ሀ. ከአጠቃላይ ቆጠራዎችና ከናሙና ጥናቶች የተሰበሰቡ መረጃዎች፡-

i. አጠቃላይ አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ (1987)፤
ii. የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት (በየዓመቱ)፤
iii. የኮንስትራክሽን ሥራ እንቅስቃሴ ጥናት በከተማ (1991)፤
iv. የማዕድንና ቁፋሮ ጥናት (1991)፤
v. የመኸርና የበልግ ወቅት የግብርና ስታቲስቲክስ ናሙና ጥናት (በየዓመቱ) (የሰብል ምርት የቤት እንስሳት፣ የዶሮና የንብ ቀፎዎች ምርት መረጃዎች)፤
vi. በገጠር የችርቻሮና የአምራቾች ዋጋ ጥናት (በየወሩ)፤
vii. የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጭ ጥናት (በ1988 እና በ1992)፤
xiii. የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት (በ1988፣ 1989፣ 1990 እና 1992)፤

ix. የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት (1989)።

x. የጎጆ/ዕደ ጥበባት ኢንዱስትሪዎች ጥናት (1989)።

xi. የአከፋፋይ፣ ንግድና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ጥናት (1989)።

xii. የእንሰት ተክል ሥርጭትና ምርት ጥናት (1989)።

xiii. የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተማ (በየወሩ)።

xiv. የአካል ጉዳተኞች የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሁኔታ ጥናት በኦሮሚያ፣ በአማራና፣ በደቡብ ሕዝቦች በተወሰኑ ወረዳዎች (1989)።

xv. የምግብ አቅርቦት ዋስትና ጥናት በገጠር (1989)።

xvi. መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት (Informal Sector) (1989)።

xvii. ናሙና የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ ጥናት (1989-1992)።

xviii. የትላልቅና የመካከለኛ ማምረቻና ኤሌክትሪክሲቲ ኢንዱስትሪዎች ጥናት (በየዓመቱ)።

xix. የሥነ ሕዝብና የጤና ጥናት (DHS) (1992)።

xx. የሰው ኃይል ጥናት (1991)።

xxi. አገር አቀፍ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ (Consumer Price Index) በገጠርና በከተማ (በየወሩ)።

xxii. የአዲስ አበባ የችርቻሮ ዋጋ ኢንደክስ (በየወሩ)።

xxiii. የመንግሥት፣ የግል፣ የንግድና የማኅበራት ሰፋፊ እርሻዎች የግብርና ጥናት (1992)።

xxiv. የሕፃናት የሥራ ስምሪት ሁኔታ ጥናት (Survey of Child Labour) (1993)። እና

xv. በ1994 ዓ.ም. ሊካሄድ ለታቀደው አገር አቀፍ የግብርና ናሙና ቆጠራ የዝግጅት ተግባራት ማከናወን ናቸው።

ለ. ከአስተዳደር መዛግብት የተሰበሰቡና የሚሰበሰቡ መረጃዎች፦

i. የኤሌክትሪክሲቲ ስታቲስቲክስ፤

ii. የአዲስ አበባ ከተማ የኮንስትራክሽን ፈቃድ፤

iii. የትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ፤

iv. የፋይናንስ ስታቲስቲክስ፤

v. የውጭ ንግድ ስታቲስቲክስ፤

vi. የጤና ስታቲስቲክስ፤

vii. የትምህርት፤ የባህልና የስፖርት ስታቲስቲክስ፤

viii. የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስ፤ እና

ix. የማዕድን ምርት ስታቲስቲክስ መረጃዎች ናቸው።

12.2 በ1994 በመካሄድ ላይ ያሉ አጠቃላይ ቆጠራዎች፤ የኢኮኖሚያዊ፤ የማህበራዊና የዲሞግራፊያዊ ናሙና ጥናቶችና ከአስተዳደር መዛግብት የተሰበሰቡ ወይም የሚሰበሰቡ መረጃዎች፦

ሀ. በመካሄድ ላይ ያሉ አጠቃላይ ቆጠራዎች፤ የኢኮኖሚያዊ፤ የማህበራዊና የዲሞግራፊ ጥናቶች የሚሰበሰቡ መረጃዎች፦

12.2.1. በግብርና ቆጠራ የሚሰበሰቡ ዋና ዋና መረጃዎች

i. ከገጠር ከግል አርሶ አደሮች የሚሰበሰቡ መረጃዎች፦

- የመኸር ወቅት ቅድመ አሰሳ (pre-harvest) የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት መጠን (የሰብል ምርት ትንበያ መረጃ)።
- የመኸር ወቅት ድኅረ አሰሳ (post harvest) የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት፣ የእርሻ ሥራ አጠቃቀም ሁኔታና የመሬት አጠቃቀም።
- የግብርና ቤተሰቦች ዲሞግራፊያዊ ባሕርያት።
- የቤት እንስሳት፣ የዶሮዎችና ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛትና የእንስሳት ተዋጽኦ ምርት።
- የእርሻ መገልገያዎች፣ የምርት ማዳበሪያዎችና ማሽነሪዎች ዓይነትና ብዛት።
- በግብርና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር ስለታቀፉ አርሶ አደሮች።
- የሰብል ምርት፣ የእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ አጠቃቀም።
- የበልግ ወቅት የሰብል ምርት መጠን፣ የታረሰ መሬት ስፋትና የእርሻ ሥራ አጠቃቀም ሁኔታ።

- ሌሎች
- – ስለሴቶች ተሳትፎ በግብርና ሥራ፣
- – ስለአፈር ጥበቃ፣
- – ስለማዳበሪያ አቅርቦትና ዋጋ ...ወዘተ ናቸው።

ii. <u>ከአርብቶ አደሮች የሚሰበሰቡ መረጃዎች:-</u>

- የቤት እንስሳት ዓይነትና ብዛት፣ እና
- የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት፣ ናቸው።

iii. <u>በከተማ በግብርና ሥራ ከተሰማሩ ቤተሰቦች የሚሰበሰቡ መረጃዎች:-</u>

- የግብርና ቤተሰብ አባላት ዲሞግራፊያዊ ባህርያት፣
- የሰብል ምርት መጠን፣ የታረሰ መሬት ስፋትና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ፣
- የቤት እንስሳት፣ ዶሮዎችና ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛትና የእንስሳት ተዋጽዖ ምርት፣ እና
- የሰብል ምርትና የቤት እንስሳት ተዋጽዖ ምርት፣ ናቸው።

iv. <u>ከመንግሥት፣ ከግል ንግድና ማህበራት ሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች:-</u>

- የመኸር ወቅት የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት፣

- የመኸር ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ፣
- የመኸር ወቅት የመሬት አጠቃቀም፣
- የቤት እንስሳት፣ የዶሮና ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛትና የእንስሳት ተዋጽዖ ምርት፣
- የበልግ ወቅት የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት፣
- የበልግ ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ፣
- የሠራተኛ ብዛትና የካፒታል መጠኑ፣ እና
- የእርሻ መሣሪያዎች የምርት ማጓጓዣዎችና ማከማቻዎች ዓይነትና ብዛት ናቸው::

12.2.2. የመካከለኛናየትላልቅ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣

12.2.3. የግብርና ምርቶች የአምራቾችና የችርቻሮ ዋጋ ጥናት፣

12.2.4. የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት፣

12.2.5. አገር አቀፍ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ (Consumers price index) በየክልሉና በአዲስ አበባ በገጠርና፣ በከተማ (በየወሩ)፣ እና

12.2.6 የአዲስ አበባ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ፣ ናቸው::

ለ. ከአስተዳደር መዛግብት የሚሰበሰቡ መረጃዎች፡-

i. የኤሌክትሪክሲቲ ስታቲስቲክስ፣

ii. የአዲስ አበባ ከተማ የኮንስትራክሽን ፈቃድ፣

iii. የትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ፣

iv. የፋይናንስ ስታቲስቲክስ፣

v. የውጭ ንግድ ስታቲስቲክስ፣

vi. የጤና ስታቲስቲክስ፣

vii. የትምህርት፣ የባህልና የስፖርት ስታቲስቲክስ፣

viii. የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስ፣ እና

ix. የማዕድን ምርት ስታቲስቲክስ መረጃዎች፣ ናቸው።

## 13. የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በአዲስ አበባ ከሚገኘው ዋና መ/ቤት በተጨማሪ በየጊዜው የሚካሄዳቸውን አጠቃላይ ቆጠራዎችና የናሙና ጥናቶች አፈጻጸም በሚገባ ለማስተባበር እንዲቻለው በየክልሉ ቢያንስ አንዳንድ የቅ/ጽ/ቤት ሲኖሩት በኦሮሚያ ክልል ስድስት በአማራ ክልል አራት እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል አራት ቅ/ጽ/ቤቶች አሉት። እነዚህም ነባር ቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኙባቸው ክልሎችና ከተሞች ዝርዝር ከዚህ በታች ቀርቧል።

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚገኙባቸው ክልሎችና ከተሞች ዝርዝር


| ተ.ቁ | ክልል | ቅ/ጽ/ቤቱ የሚገኝበት ከተማ | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|---|
| 1 | ትግራይ | መቀሌ | 04-40-04-88 |
| 2 | አፋር | አሳይታ | 03-55-02-15 |
| 3 | አማራ | ባህርዳር | 08-20-48-00 |
| 4 | " | ደብረ ብርሃን | 81-26-19, 81-35-74 |
| 5 | " | ደሴ | 03-11-66-54 |
| 6 | " | ጎንደር | 08-11-08-38 |
| 7 | ኦሮሚያ | አምቦ | 36-22-31 |
| 8 | " | አስበ ተፈሪ | 05-51-03-50 |
| 9 | " | ጎባ | 06-61-01-09 |
| 10 | " | ጅማ | 07-11-12-50 |
| 11 | " | ናዝሬት | 02-11-36-23 |
| 12 | " | ነቀምት | 07-61-16-45 |
| 13 | ሶማሌ | ጅጅጋ | 05-75-02-75 |
| 14 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | አሶሳ | 07-75-01-61 |
| 15 | ደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች | አርባምንጭ | 06-81-00-61 |
| 16 | | አዋሳ | 06-20-03-09 |
| 17 | " " " " | ሆሳዕና | 06-55-00-81 |
| 18 | " " " " | ሚዛን ተፈሪ | 07-35-04-25 |
| 19 | ጋምቤላ | ጋምቤላ | 07-51-00-51 |
| 20 | ሐረሪ | ሐረር | 05-66-06-91 |
| 21 | አዲስ አበባ መስተዳድር | አዲስ አበባ | 18-49-44, 62-38-15 |
| 22 | ድሬዳዋ ካውንስል | ድሬዳዋ | 05-11-39-34 |

## 14. አዲስ የተከፈቱ የግብርና ቆጠራ ጽ/ቤቶች

በ1994 ዓ.ም. ባለሥልጣኑ ከሚያካሂዳቸው ተግባራት መካከል አብይ የሆነው አጠቃላይ የግብርና ቆጠራ ነው:: ይህንንም ተግባር ለማከናወን ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰው ኃይል (13,000 መረጃ ሰብሳቢዎች፣ 3,000 ተቆጣጣሪዎች፣ ...ወዘተ) እንዲሁም በጣም በርካታ የሎጂስቲክስ፣ የመስክ መሣሪያዎች፣ ቁጥራቸው በጣም ብዙ የሆኑ የተለያዩ ቅጾችና ፎርሞች፣ የአሠራር መመሪያዎች፣ የመስክ ተሽከርካሪዎች፣ ... ወዘተ ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል:: በመሆኑም ይህን ግዙፍ የሆነ ፕሮጀክት ለማስፈጸም ከላይ በተጠቀሱት 22 ቅ/ጽ/ቤቶች ብቻ ማከናወን የማይቻል መሆኑን በመገንዘብ ተጨማሪ 25 የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (የግብርና ቆጠራ ጽ/ቤቶች) ተከፍተው የቆጠራው ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል:: በመሆኑም እነዚህ የግብርና ቆጠራ ጽ/ቤቶች የሚገኙባቸው ክልሎችና ከተሞች ዝርዝር ከዚህ በታች ቀርቧል::

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚገኙባቸው ክልሎችና ከተሞች ዝርዝር

| ተ.ቁ. | ክልል | የቆጠራ ጽ/ቤቱ የሚገኝበት ከተማ | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|---|
| 1 | ትግራይ | አክሱም | 04-75-19-22 |
| 2 | " | እንዳስላሴ | 04-44-02-73 |
| 3 | አማራ | ደብረ ማርቆስ | 08-71-13-57 |
| 4 | " | ደብረ ታቦር | 08-41-09-82 |
| 5 | " | ከሚሴ | 54-04-29 |
| 6 | " | ወልድያ | 03-31-17-30 |
| 7 | ኦሮሚያ | አሰላ | 02-31-32-53 |
| 8 | " | ደደር | |
| 9 | " | ደምቢዶሎ | 07-55-07-09 |
| 10 | " | ፍቼ | 35-08-97 |
| 11 | " | ጊኒር | 06-64-01-82 |
| 12 | " | ጊምቢ | 07-71-06-74 |
| 13 | " | መቱ | 07-41-24-17 |
| 14 | " | ነጌሌ | 06-45-05-25 |
| 15 | " | ሻምቡ | 06-66-00-92 |
| 16 | " | ወሊሶ | 41-08-49 |
| 17 | ኦሮሚያ+ሶማሌ | ሞያሌ | 06-44-00-52 |
| 18 | ደቡብ ብ/ብ/ሕ. | ቦንጋ | 07-31-02-15 |
| 19 | | ዲላ | 06-31-24-52 |
| 20 | " " " " | ዱራሜ | 06-54-00-29 |
| 21 | " " " " | ጂንካ | 06-75-01-05 |
| 22 | " " " " | ሶዶ | 06-51-23-46 |
| 23 | " " " " | ዋካ | |
| 24 | " " " " | ወልቂጤ | 30-10-88 |
| 25 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | ፓዌ | |



የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
አንፃራዊ ሥፍራ ካርታ
ደጎል
አደባባይ
ሲኒማ
ኢትዮጵያ
ኢ.ንግድ
ባንክ
ቴዎድሮስ
ቅርንጫፍ
ሆቴል
ጣይቱ
ሆቴል
ወረዳ 2
መስተዳደር
ጽ·ቤት
ቸርቸል ጎዳና
መንገድ
ጋንዲ
ንግድ
ባንክ
ጋንዲ
ቅርንጫፍ
ፓርክ ሆቴል
ጠቅላይ ግምጃ ቤት
ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ
ባለሥልጣን
ወደ አራት ኪሎ
ወረዳ 2 ፖሊስ ጣቢያ
ወደ አሮጌው ቄራ